# የተኛው ኣንበሣ

ከዓሣዬ

ኮቴው ኣይሰማ ዱካው ኣይታይ
እየተከታተለ ዓይኑን ሣይነቅልበት ካለመው ግዳይ
ድንገት ሲነድፋቸው ፡ ልክ እንደ ተባይ
በምሥራቅ በምዕራብ በሰሜን በደቡብ ዙሪያውን ሲቃኝ
ትኩሣቱ በዝቶ ወላፈኑ ንሮ ብርክ ሲለቅባቸው
ሞቷል ጠፍቷል ያሉት ተሰደደም ያሉት ቅዠት ሆነባቸው ።

የተበጠሰውን እየቀጣጠለ
የተበተነውን ዞሮ እየለቀመ
በፍኖት እራዲዮ ፡ ሕልቆ መሣፍርትን እያሰባሰበ
በኣንድነት ዙሪያ ላይ እያፈጣጠመ
የተዳፈነዉን የእሣት ዕረመጡን እፍ እፍ እያለ
ወያኔን ሊያነደው ክብሪት እየጫረ ፡
የዓመፅ ግለቱን እያቀጣጠለ ፡ ኣድማሱን ኣሠፋፍቶ
ኢሕኣፓ ኣጎልብቷል ፡ በዳር ብቻ ሣይሆን ከመሃሉም ገብቶ
መልክ መልክ እያሠያዘ ፡ ላይቀሬው ትንቅንቅ በድርጅት ኣቅፎ ።

ኣዎ ደሥ ይበለን !
ኢሕኣፓ እንደሆነ ፡ ጋራ ሸንተረሩን ዱሩን ተንተርሶ
ከሰፊው ሕዝብ ጋር እጅና ጓንት ሆኖ
በቆላና ደጋ በደቡብ ሥር ሰዶ
እንደ ሃረግ እሬሣ ዙሪያ ተጠምጥሞ
በወልቃይት ጠገዴ ቋራና ኣርማጭሆ
ኣመጹን ፈር ሊያሥይዝ ተከዜን ተሻግሮ
በኣሩሲ ሃረርጌ በባሌ ኦሮሞ
በምዕራብ በሸዋ በጎጃም በወሎ
ባለ ነፍጥ ሰብሥቦ ፡ በከፋ ወለጋ በሲዳሞ ጋሞ
ታምቆ የነበረው የተኛው ኣንበሣ
ከዕንቅልፉ ነቅቶ ፡ እነሆ ሰማነው ከዕሩቁ እያገሣ

*ዝግጅት በማድረግ !*

*የኣባቱን ኣገር ጠላት ፡ በነጎድጓድ መብረቅ ሊያሣየው ኣበሣ ! ።*

*ታድያ !*

*እንዲህ ባለው ጽናት ኣገርን ሊታደግ*

*ዕቅዱ ተነድፎ ዝግጅቱ ጡፎ ሲቀረው መተግበር*

*መፍትሄን የሚሻ ትልቅ ችግር ኣለ ፡ እንደ መርግ የሚከብድ ።*

*ኣጥንቱን ከሥክሶ ደሙንም ኣፍሥሶ*

*ታግሎ ለመሰዋት ውድ ሕይወቱን ሰጥቶ*

*ሆሆ ብሎ ለመግባት በገፍ ተሰልፎ ፡*

*ከእግር እሥከ ኣናቱ የታጠቀን ጠላት*

*ከሥሩ መንግሎ ነቃቅሎ ለመጣል*

*የገንዘብ እጥረት ችግር ፡ ኣቅሙን ውሱን ኣርጓል ።*

*ሥለዚህ !*

*ኢሕኣፓን ለማጎልበት በገንዘብ ኣቅማችን*

*ጥረት ካላደረግን በዜግነታችን*

*እንደ ዔሊ ከሆነ ፡ በጣም ያዘገመ የትግል ጉዞኣችን*

*ድሉ ይርቅና እየተራዘመ ፡ ሥቃይ ሰቆቃችን*

*ወያኔም ይገዛል ፡ እየተንገዳገደ ሣንወድ በግዳችን ።*

*እናም ቀኑ ሣይመሽ ፡ ከእንቅልፋችን ነቅተን*

*ከጠላት እጅ ወድቃ ፡ ኣገር ሣትበተን*

*ኢትዮጵያን እናድን ፡ እሥቲ የድርሻችንን ፡ በነፍሥ ወከፍ ከፍለን ።*

*የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለ ጥርጥር ያቸንፋል*

*04/23/2016 G C.*